**ዲኮንስትራክሽን፥ ነገረ ሞት፥ ንቡር ጠቃሽነት እና ፖለቲካዊ አሊጎሪ - በ“የስንበት ቀለማት”**

ቢኒያም አቡራ

በአፍሪካ ትልቁ የሆነው ይህ ረዥም ልቦለድ በ10 ክፍሎች ተከፍሎ፥ በ46 ንዑስ ታሪክ ውስጥ ከ60 በላይ ገጸባሕርያት ተዛንቆ፥ በ8 ቀለማት ተወክሎ፥ ተቀንብቦ፥ በፍርርቅ የአተራረክ መንገድ የቀረበ ነው። ምትክ፣ ድንግልና፣ በድንግልና ማርገዝ …

የስንብት ቀለማትዋ ምትክ፥ ድንግልናዋ እንደ "ሔራና አፍሮዳይት" ታዳሽ አይደለም። ምትክ፣ እንደ ቡድሃ እናት ልጇን በድንግልና ከወለደች በኋላም አትሞትም። እንደ ቅድስት ድንግል ማርያም ኢየሱስን በድንግልና ከወለደች በኋላ ሌላ የማትወልድ ናት ለማለት እርግጠኝነት ይጎድለናል (አዳም ቀጣዩን ምናብ ለተደራሲው ትቷልና) ። ግን አንድ ነገር እንገነዘባለን። በዓለማችን የተከሰቱ ዲበ-ሰዎች ከድንግል የሚወለዱ ናቸው።

“በሀገራችን ለተንሰራፋው *ሥራይ፥ መፍትኼ-ሥራይ የሚያመጣው ከድንግሏ ምትክ የሚወለደው የስንዝሮ ልጅ ይሆን?*” ብለን እንድንጠይቅ ያደርጋል። የመጽሐፍ ቅዱሱ አይሁዳዊው ዮሴፍ እና የደምቢዶሎው ዮሴፍ እንዲያው የስም መመሳሰል ብቻ ነውን? እትየ እልልታስ “እመቤታችን፣ ቅድስት፣ ተስፋችን …” ለምን ይሏታል? በከብቶች በረት የተወለደው መሢሕ ለአይሁድ፣ ለሰማርያ እና ለአሕዛብ መፍትኼ-ሥራይ እንደ ኾነ ሁሉ፥ ሙሉ ለሙሉ ተሠርቶ ባላለቀው የዮሴፍ ቤት ውስጥ፥ የመንኮብያው ልጅ ሲወለድ፥ በጎችና ላሞች መከሰቱ የወንጌላቱ መጻሕፍትን አያስተዝትምን? ኢየሱስ በበረት የተወለደው መልካም እረኛ እንደ ሚኾን ለመጠቆም ይኾን? የምትክ ልጅ ባላለቀ ቤት የተወለደው ቤቱን ሠርቶ ሊያጠናቅቅ ይኾን? የዮሴፍ ዐዲሱ የሕክምና ተቋምስ ስለምን ቤዛ ክሊኒክ ተባለ? ስንዝሮ የሰጣት ወርቅ … የጉሊቱን ጠረን የቀየረው መዓዛዋ … ዮሴፍ ባልጠፋ የጉልት ዕቃ ዕጣን መግዛቱ … ሰብአ ሰገል ለረቡኒ ካመጡት ወርቅ፥ ዕጣን፥ ከርቤ ጋር የሚያስተሳስር ነገር ይኖረው ይሆን? ወርቅ የጽሩይ (የጠራ፣ ንጹሕ)፣ ከርቤ የተለየውን በፍቅር አንድ የማድረግ እንዲሁም ዕጣን ደግሞ የተስፋ ትዕምርት አይደለምን? እዚህ ላይ ስንዝሮ የአማልክትና የንጉሣዊ ዘር ቅይጥ መኾኑ ደግሞ እናክልብት እንዴ? ጋሽ አዳምን ቅይጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንቡር ጠቃሽ (Mixed biblical allusion) ነው ልንለው እንችል ይኾን?

ከሸዋው ንጉሥ ሳህለሥላሴ ቀዬ አንዲት ገረድ አስደማሚ ሕልም በማለሟ ምክንያት ከልጃቸው ጋር እንድትተኛ መደረጉን የአብዬ መንግሥቱ ወላጅ አባት፥ አለቃ ለማ ኃይሉ አስቀምጠውልንም የለ? እዚህ ጋር የስንብት ቀለማት ላይ ሲኖዳ ሕልም ማየቱን ስናስገባው ደግሞ አንድ ነገር ብልጭ ይልልንም የለ? ምትክ በሕልሟ የእሳት ወተት ስትሸና ማየቷን “ፀሐይ ከብልቴ ወጣ!” ካለችው ጋር የሚያስተሳስር ገመድ ይኖረው ይኾን? ደሞስ “እንደ እሳት ኃይለኛ እና እንደ ወተት ገር የሚሆነው surrealism ወለድ ነው!” ማለትስ ይቻለናል?

የመጽሐፉ የገጽ ሽፋን ላይ ካሉት ውስጥ መሐል ላይ ያለችው፣ ዓይኖች ሁሉ ወደሷ የሚያማትሩባት፣ ጥቁርነት በሚታገለው ወርቃማ ቀለም ላይ የተሰየመችው ማን ናት? ምትክ ናት ማለት እንችል ይሆን? ለምን እሷን ያይዋታል? ለምንስ ተስፋ ያሳድርቧታል? እትየ እልልታ “ድመቶች ሀገር ለምን ሳንባ እሆናለሁ? ከሆነልኝ ውሻ፣ ካማረልኝ መጥማጥ መሆን እንጂ” ብለው እንደ ነውር የተቆጠረውን ጉርሻ ሲሸጡ፣ ከታመሙበት ራስ ምታት እንዴት በምትክ ጠረን ተፈወሱ?

ፊያሜታዊነት ዲኮንስትራክት ተደርጎ ይኾን?

ፊያሜታ ሲባል ወደ አእምሯችን ምን ይመጣል? ከአንድ ገጸባሕርይነት ከፍ አላለችም? በስሟ ተዘፍኗል … ስሟን ከስሙ ያዋሃደ ፊልም አቡጀዴ ላይ ተሰጥቷል … ቲያትራችን ውስጥም ገብታለች። ለአያሌ የማኅበራዊ ድኅረ ገጽ ተጠቃሚዎች የጭምብል ስም ቋት ኾናለች። የምድረ ሐማሴን እንስቶችን በሞላ እንደሷ ያሉ እንደ ኾኑ ማሰብ ከጀመርን ሰነባብተናል። በኅያሲዎቻችንም ዘንድ ሮማንን እንደ ኢትዮጵያ ፊያሜታን እንደ ኤርትራ የመፈከር ዝንባሌ ይታያል፤ ወደ ሰፊው ሕዝብም ተጋብቷል። ፊያሜታ አሁን አንድ ተራ ስም ከመኾን ተሻግራ ራሷን የቻለች ትወራ ሆናለች። ከትንሽ ነበልባነት ወደ እቶን እሳት አድጋለች። ፊያሜታ ተለጥጣ ፊያሜታዊነት የተሰኘ የተዋቀረ ኅልዮት ጋር ደርሳለች። በኔ እምነት ይኼ ውቅር በ"የስንብት ቀለማት" ዲኮንስትራክት የተደረገ ይመስለኛል። ምኒልክን እንደ ጸጋዬ ኃይለማርያም ሳንቆጥር፥ ሳፍሮንን ችላ እንደ ተባለችው ሮማን ሳንወስድ የፊያሜታ ግብርን ከምኒልክ ጋር በአንድ መም ላይ በማስኬድ ብቻ ማወቅ ይቻላል። ፊያሜታዊነትን ጋሽ አዳም ዲኮንስትራክት እንዳደረገ በግልጽ ተቀምጧል።

በርግጥ ድኅረ ዘመናዊ ሥነጽሑፍ የደራሲነቱን ባለቤትነት ለማኅበረሰብ ውቅር (social construction) ስለሚሰጥ ለምን ፊያሜታን ዲኮንስትራክት ሊያደርጋት እንደ ፈለገ የመጠየቅ መብት ይነፍገናልና ምላሹን ከጽሑፉ አውደ ንባብ ለማግኘት መታተር ይጠበቅብናል። ለዚህም ምላሽ የፊያሜታ፥ የምኒልክ ባዩ፥ የዮሐንስ ወላይሶ፥ የውሻዎቹ፥ የቤላ ፍራንኮ፥ የጸጋ፥ ጋዜጠኛው ፀሐይ የማነ … ተረኮችን በአንክሮ ማጤን ይሻል። ፊያሜታዊነት እና ዲኮንስትራክሽን ጋር ለመድረስ የውሻዎችን ታሪክ እንንጠልጠል እስኪ።

የውሻዎቹን ታሪክ እንደ ፖለቲካዊ አሊጎሪ (political allegory) ብንመለከትስ? ቀስቶ የተሰኘው ውሻ "ከብት ከከለከሉን ሬሳቸውን እያወጣን መብላት ነዋ………የሚረባ ሬሳ ካላቸው ነው ደሞ። አንጎል አልነካም ያኔ። የእነሱ ደደብነት እንዳይጋባብኝ። (504)" እሚለውን በዋዛ ማለፍ ይቻለናል? የያ ትውልድ አባላት በኮድ እንደ ሚግባቡት ሁሉ ስንዝሮ ቀስቶ የተባለውን ውሻ የሚያገኘው ከሳምራዊው በተቀበለው ኮድ መኾኑ አንዳች ፍንጭ አይሰጠንም?

ቀስቶ አንዱን ነጭ ቡችላ ይጠራውና "እስኪ አንድ ጎድን አጥንት አምጣልኝ" ሲለው ደረቅ እንጨት ይዞ ይመጣል። ዐዲሱ የውሻ ትውልድ ሣር እንዲበላ በመደረጉ፥ ሥጋን ከእንጨት አለመለየቱን ቀስቶ የተባለው ውሻ ለስንዝሮ ያስረዳል - ከላይ የቀረበውን ታሪክ ያዙልኝ። ዮሐንስ ወላይሶ ደግሞ በሌላ ገጽ ላይ እንዲህ ይላል፡- "ሁሉም ያለ ምሕረት ያለ በቂ ትንታኔ የዛሬውን ወጣት ያማሉ። እነዚህን ዕድለቢስ ጠማማነትን የተረከቡትን ጉብሎች ሲከላከሏቸው የምናየው ጥቂቶችን ናቸው። 'ወጣት ድሮ ቀረ' አንዱ ወሬአቸው ነው። 'ድሮ ሲሉ እኛ' ማለታቸው ነው። ይሄ 'ድሮ የተባለው ቃል የማይሞት ነው። ይኼም … ሕመም ነው። "(430) ዐዲሱ የውሻ ትውልድ እና ዐዲሱ የሀገራችን ትውልድ በሁለቱ "ያ ትውልድ" አልተሳሰረምን? ሳምራዊው የተባለ ውሻ ስንዝሮን ሲሰናበተው "ንጹሕ ሰው የለም ንጹሕ ውሻ የለም - ተደበላልቀናል" ያለው ጥቁምታ ሊሰጠን አይደል?

የውሻዎቹን ታሪክ በአሊጎሪካዊ መነጽር ሳየው፥ ዮሐንስ ወላይሶ ለኔ ሳምራዊው እንደ ተባለው ውሻ ነው። ዮሐንስ ወላይሶ ከመጽሐፉ ውጪ ኾኖ ሕዳግ ላይ እንደሚያኄሰው፥ ሳምራዊውም ከአዲስ አበባ ውጪ ኾኖ የአዱ ገነትን ጅማትና ቅልጥምን ይለያያል፤ ያትታል። ውሻ ኾኖ ሳለ አውቶብስ የሚባለውን ለስንዝሮ ሲያስረዳ "ሳር አይግጥም እንጂ … በቅሎ … ቢጤ ነው - ባይበላህም ይገጭሃል - ስንቱ ወዳጄ አልቋል" ሲል እናገኛለን። አውቶብሱ ሀገር በቀል ያልኾነው የጨፍጫፊው ትዕምርት (symbol) ይኾንን? ሳምራዊው ይለጥቃል "አብዮት - ብዙ ሰዎች በኅብረት ለንቦጫቸውን ሲጥሉ ነው … ዘመናዊ (ማለት ደግሞ) የሰው ጉዳይ ይናቅና ቁሳቁስ ከሰው በላይ ሲሰለጥን ነው - ዘመናዊነት በረታ ሲባል ሥጋ ጠፉ" ሲል እናገኘዋለን። ሳምራዊው፥ የውሻው ዮሐንስ ወላይሶ እንደ ማለትም አይደል? እንለጥቅ!

አሊጎሪካዊ አንድም ዘይቤ አንድም የፍቺ ሥርዓትም አይደል? ክርክሩን ሊጋሽ ብርሃኑ ገበየሁ እና ሊጋሽ ዓለማየሁ ሞገስ ትተን አንድ አፍታ የሁለቱንም ሐሳብ እንቀበል። ውሻ በአሊጎሪካዊ ዘይቤ እንደ ታማኝ አይደል? ታማኞች ለከሃዲዎች ይመቹም የለ? በተለይ እንደ ምኒልክ ያሉቱ። ውሻ ከ25 ዓመት በኋላ ጌታው ቢመጣ የጌታውን ጠረን መች ይረሳል? ጭራውን እየቆላ ስብሰባ እስኪያልቅና ጌታውን እስኪያገኝ ይንቆራጠጣል እንጂ። ምኒልክ ለክህደት የተመረጠ ቡችላ ነበር። አስር ጊዜ ተክዶ አስር ጊዜ እስኪካድ የሚያደገድግ የፊያሜታ ችሎ-ማደር ነው ምኒልክ። እውነተኛ ንብረቱን (ሥጋ) ነፍገውት፥ ወደ ውጪ እየቸበቸቡበት፥ በዝምታ ራሱንም ኾነ ልጆቹን ሣር እሚያለምድ ቀስቶ - ነው ምኒልክ።

ዮሐንስ ወላይሶ እና ምኒልክ የያ ትውልድ አባል ናቸው። ቀስቶ እና ሳምራዊው የተባሉ ውሾችም የቄራው ዓመፅ አባልም መሪዎችም ናቸው። የያ ትውልድ እንቅስቃሴዎች አከሻሸፍ በውሾቹ ዓመፅ ውስጥ ተዘይቧል። ውሾቹ አጥር ሰብረው ሲገቡ የሚያስቆማቸው አልነበረም። ነገር ግን የመሪዎቹ ደካማነት፥ የተከፋፈለ ግብና ድርጊት ውጥኑን አኮላሽቶት የስንት ሰላማዊ ቡችላ ደም ፈሰሰ? ከዚህ የትውልድ ክስረት በኋላ፥ ቀስቶ እዚያው አዲስ አበባ ጎመንኛ፣ ሣር በሌ ኾኖ በድብቅ ሲኖር፥ ሳምራዊው ደሞ አራስ ተከትሎ፥ ዐዲስ የሚወለድ ተስፋ ዘንድ ሄዶ በነጻነት ይኖራል፤ በዓል ጠብቆም ቢኾን ሥጋ እየበላ። ልክ እንደዚሁ ምኒልክ በዛጎሉ ውስጥ ተጠቅልሎ ሲኖር፥ ዮሐንስ ወላይሶ ግን የነጻነት አየር ይተነፍሳል። ሳምራዊው ነጻነቱን መርጦ ሲሄድ ቀስቶ ግን "ከማውቃቸው ወዳጆቼ መለየት አልፈለግኩም" (ገጽ 505) ብሎ ይቀራል። በሚወዳቸው ዛጎል ይሸበባል። ቀስቶ እና ውሻዎቹ ተደብቀው ሲኖሩ ሥጋ የሚባል ነገር በዓይናቸው አልዞረም። ሊያገኙ ከሞከሩ ሞት ነው የሚጠብቃቸው። በሕይወት መቆየት ከፈለጉ ጎመንኛ፣ ሳር በሌ፣ ገጤዎች መኾን አለባቸው። የዚህ ባርነት ተገዢ መኾናቸውን የሚያሳይ አረንጓዴ ጥብጣብ፥ አንገታቸው ላይ ማንጠልጠል ግዴታቸው ነው። ልክ እንደዚሁ ፊያሜታና ግብረአበሮቿ እንደነ ምኒልክ ዓይነቱን የጎመንኛ ማህተም አትመውባቸዋል። "የሥጋ ጥያቄ እጠይቃለሁ!" - ቢሉ የስንብት ቀለም ይቀባሉ።

የምኒልክ ዛጎል ፊያሜታ ነበረች። ይህ ዛጎል ስህተት መኾኑን ምኒልክ ባለመቀበሉ፥ ሥጋ እንደ ማያገኘው ቀስቶ ተመስሎ በጉድጓድ ለመክረም ተገደደ። ዛጎሉ የተሠራው በእነፊያሜታ ነው። የሱ የፖለቲካ ትግል የተዘወረው በራሱ ሳይኾን በእነርሱ ነበር። እዚህ ዛጎል ውስጥ ባለቤቱ ሳፍሮን እና ልጁ ቤርሳቤህ ፈጽሞ የሉበትም። ውሻዎቹ ከጮኹ እንደ ሚረሸኑ ሁሉ የምኒልክም ጩኸትን እንደ ዋዛ አይታይም፤ በእነ ፊያሜታ። ለዚያም ነው ቀስቶ "አሁን ማታ አዲስአባ ከተማ ውስጥ የውሻ ጩኸት አትሰማም። አንዱ በድንገት ቢጮህ የሚከተለው የለም። ድሮ ቀረ። ዛሬ አንዱ ጮኾ የሚከተል ሌላ ውሻ ከተሰማ ሁለቱም ታድነው ይገደላሉ" የሚለው። ፊያሜታ ከአሜሪካ ከ25 ዓመታት ቆይታ በኋላ እንደ መጣች እነቤላን ጆሮ ጠቢ አድርጋ የሾመችው፥ ምኒልክ ሥጋ በል ወይም ሣር በል መኾኑን ለማወቅ ነው። ፊያሜታ ትንሽ ሰከን ያለችው ምኒልክ ከጎመንኛነቱም በላይ በአንገቱ ላይ እንደ ውሾቹ ባንጠለጠለው መተማመኛ ነው። ዮሐንስ ወላይሶ ግን ፍቼ እንዳለው ሳምራዊው በነጻነት መጮህ ይችላል። ምክንያቱም የትውልዱን ስህተት አፍረጥርጦ ለማተትም ኾነ ስህተቱን ለመንገር አያመቻምችም(አያፈገፍግም)። ፊያሜታ የዘመናቸው ስህተት መኾኗን ዮሐንስ ወላይሶ ያምናል። የግሉን ፊያሜታንም ለመንገር ይደፍራል። "በተለያየ ጥበብ ራሱን ሊያድን የሚሯሯጥ አለ። እኔ አልሯሯጥም። ራስ ወዳድነቴን ሁሉ ሰው እንዲያየው አደርጋለሁ። How foolish I am." ሲል እናገኘዋለን።

በዚህ ውስጥ ፊያሜታዊነት ዲኮንስትራክት ተደርጓል። ፊያሜታ ሥጋን ከእንጨት እና ከድንጋይ የማይለይ ትውልድ እንዲፈጠር ታትራ ተሳክቶላታል። በሁለት ቢለዋ ትበላለች። አይደለም ለሥጋ ቀርቶ ወዳጁን ለመጣራት የሚጮኽ ውሻ ካለ ድምፁን ትሰልባለች። ሣር በል፣ ገጤ ያልኾነውን ወይ በገዛ ወገኑ ታሳድናለች፤ ወይ በነጭ ምሁራን ሾተላይ ውስጥ ታሳልፈዋለች። ለሷ እንደ ሚያሸረግዱ መተማመኛ

የሚኾነውን አረንጓዴ ጥብጣብ አንገታቸው ላይ ያላንጠለጠለውን ወይ ታጠምቃለች አልያ ታንጠለጥላለች። የመታገያ አጀንዳ ሰጥታ፣ ከዳር ቆማ፣ ጨዋታው ሲጠናቀቅ ከባለድሉ መንጋጋ ውስጥ ሽንፈትን ሞጅራ፣ ድሉን ትሰርቃለች። ክርስቶፈር ክላፋም "Ethiopia pulled defeat from the jaws of victory." ብለውም የለ? ተዘራፊው ማን እንዳራቆተው እንዳያውቅ፣ ባልንጀሮቹን አሰልፋ ወገኑን እንዲዠብጥ አደገኛ ልምጭ ሰጥታ፣ ሰለሜ ሰለሜ ታጫውተዋለች። ሽልን ፖለቲከኛ አድርጋለች። "ዘመናዊ ሜንጦ እና ሥጋ ምንም ዓይነት ትስስር የላቸውም!" ብላ ሥጋ ትነሳለች። ፊያሜታዊነትን እያሰረጸች፣ ሮማንነትን፣ ሳፍሮንነትን እንደ ሙየሌ ትመነግላለች። "የተወጋ በቅቶት ቢ(ተ)ኛ - የወጋ መች እንቅልፍ አለው? - የጅምሩን ካልጨረሰው" እንዳለው ሎሬቱ ከ25 ዓመታት በኋላ መጥታም ምኒልክን በዛገ ጦሯ ትጠቀጥቀዋለች። በዚህና መሰል ግብሯ እና ታሪኳ ጋሽ አዳም ፊያሜታዊነትን ዲኮንስትራክት አድርጓል ብዬ አስባለሁ።

በ"የስንብት ቀለማት" ላይ፣ ፊያሜታዊነት እንደ መስቀል ተሣላጢንነት ቀርቧል። መስቀል ተሣላጢን ከላይ መስቀል ከታች ጉድጓድ የሚቆፍር የሾለ አንካሴም አይደለ? ከሥር ጉድጓድ ምሶ ከላይ ድግስ እንዳበላው ንጉሥ፥ በክሕደት ሠላጢን ጨብጦ የእምነት መስቀል ማሳለም ነው - ፊያሜታዊነት። ከላይ ለሴቶች የቆመ "ኤንጂኦ"፣ ከሥር ደግሞ ንጋትን ማስለቀስ፥ ሳፍሮንን የቁም-መበለት ማድረግ ነው ፊያሜታዊነት። ከላይ የሕጻናት ጉዳይ ግብረሰናይ ድርጅት ዳይሬክተርነት፣ ከሥር የንጋትን ልጅ ደመወዝን ማኮላሸት፣ የሳፍሮንን ልጅ ቤርሳቤህን ማቀጨጭ፣ የእነ ቀስቶን ቡችላ ሥጋ መንሳት ነው - ፊያሜታዊነት።

**ነገረ-ሞት**

ፍሬድሪክ ዊልሃም ኒቼ የሚኖርለት "ለምን" ያለው የትኛውንም "እንዴት" ይቋቋማል የሚል ታዋቂ ትወራ አለው። በኔ ዕምነት ሻምበል ጉተማ፣ ዘወዲት ዘመነ እና ምኒልክ ባዩ የሚኖሩለት ምክንያት አሸለቦ በመግባቱ ነው መሰንበትን የተሰናበቱት። ምኒልክን በሽታ ሳይኾን የፊያሜታ "አላውቅህም" የተሰኘው አረር ነው የገደለው። የሚኖርለት ለምኑ ሳፍሮን፣ ቤርሳቤህ፣ ንጋት እና ደመወዝ ሳይኾኑ ፊያሜታ ነበረች። ልጅነቱን ወጣትነቱን ገብሮላታል። በጎልማሳነቱም በሳፍሮን ገላ ፊያሜታን ነበር ሲያቅፍ የከረመው። እዚህ ጋር "እሳት ወይ አበባ" ለምን ትዝ አለኝ? ምኒልክ በስንዝሮ ዘንግ አናቱን ተመትቶ ወደ ሕይወት ተመልሶ ይናዘዛል። ተመልሶ ግን ይሰናበታል። የያ ትውልድ አባላት በቋፍ ላይ ስላላችሁ እንደ ዮሐንስ ወላይሶ ስህተታችሁን ተናዘዙ ለማለት ይኾን?

ሻምበል ጉተማን መካንነቱ አልያም በጦር ሜዳ ውሎው አካለ-ስንኩል መኾኑ በቀጥታ የሚኖርለትን ለምን አልቀማውም። "የጀልዴሳን አወዳይ ጫት በጎልማሳነቱ ከሲያድ ባሬ መንጋጋ አላቅቆ፥ እነርሱ አፍ አስገብቶ፥ መርቅነው በፈዘዙ ዓይኖቻቸው እያዩ ጣል ጣል ሲያደርጉት ግን መኖሩ ትርጉም አጣ። "እኔ ወታደር ነኝ፤ ሞትን አልፈራም ..." ይላል። በክብሩ ሲመጡበት ግን "የትኛውንም እንዴት" መቋቋም አልቻለም። ሐይቅ ውስጥ ገብቶ ሰጠመ። አሪስቶክራት ኅብረተሰብ ዘንድ እንዳሉት "ሜጋሎቲሚያ" ክብርን ፈልጎ አይደለም ክብሩን ሲያጣ የሞተው። ለሀገሩ የተዋጋውም የአርስቶትል ሪፐብሊክ ላይ እንደተጠቀሰው፥ "ታይሞስ" በተሰኘው የዕውቅናን ክብር የሚፈልገው የነፍስ ክፍል ገፍቶት አይደለም ከሞት አፍንጫ ሥር የገባው። ለእናት ሀገሩ ክብር ብሎ እንጂ። በእናት ሀገሩ ክብር ውስጥ ነው የእሱ ክብር ያለው። አንድ ዓይኑን እና እግሩን ለሰዋለት ኅብረተሰብ መጣ። ግን የተቀበሉት በግልምጫ ነው። በአሽናፊ እና ቢጤዎቹ "የሚኖርለት ለምኑ" ስትደፈጠጥ፥ ከዚያ ወዲህ ኑሮ አላሻውም። ሻምበል ጉተማ የኢትዮጵያ ወታደር የሚለው ቀርቶ "የደርግ ወታደር" በሚል ንጥል ገፊት ለቀመሱት ማስታወሻ ይኾን? ፒየር ማሻሪ "ሥነ ጽሑፍ ለተጻፈበት ዘመን ጥበባዊ አንደበት ነው!" ይልም የለ?

ዘውዲትም ራሷን ታሰናብታለች። የምትኖርለት ለምኗ የተሳሰረው ናሆም ከተባለ ባለትዳር ጋር ነበር፤ ሲበጠስ ለመኖር ምክንያት አጣች። የልጅ ሞት ምንኛ እንደሚያንገበግብ በማሰብ ራሷን ለቤተሰቦቿ ስትል ለማቆየት ለአፍታ እንኳ አላሰበችም። "ለራስ ግድያ ከሞት ናፍቆት ይልቅ የሕይወት ጥላቻ ነው ቅርቡ፤ የጠሏት ሕይወት ውስጥ ተቀምጠው ከመጠበቅ እርሱ ወዳለበት መሄድ።" ይልም የለ ጋሽ ቴዎድሮስ ገብሬ። ዘውዲት፣ ቀይ ቀለም በበዛበት የወርቁ ሥራ ላይ በገላዋ ስዕሉን በማተም እንደ ምትሞት ንግርት መሰል መልዕክት አስቀምጣም አልነበር? ንግርቱን ፈጸመች። እርቃኗን እንደ ክርስቶስ ተዘርግታ ሞተች። ዘውዲት የማን ትዕምርት ናት? ማንንስ ልትዋጅ ነው?

የምትክ ወላጅ አባት የኾነው ደረሰ ዋቄን ለሞት ያበቃው ጥልቅ ኀዘን ነው። ጥልቁ ኀዘን የመጣው በልጁ በተስፋዬ ሞት ነው። የሚኖርለት ለምኑ ተስፋዬ ነበር፤ ምንም እንኳ ተስፋዬ የአብራኩ ክፋይ ባይኾንም። ተስፋዬ ቀይ አፈር ላይ በማያውቀው ጉድ የቀይ ሽብር ሰለባ ኾነ። በዚህች ምድር ስንት ተስፋዬዎችን አሰናብተን? የስንት ደረሰዎችን፣ የስንት ላስታዎችን፣ የስንት ምትክዎችን … ሕይወት አበላሽተናል? ለእምቦቀቅላው ኢብሳ ሞት ማነው ተጠያቂው? ፋርማሲስቷ ኀብስት ወይስ ዶክተር ዮሴፍ? ለኢብሳ ስንብት ተጠያቂዋ ቅናት ሥጋ ለብሶዋ ሳላይሽ ብቻ ናት? በበሬው ለመወጋት በሬው ብቻ እንዴት ጥፋተኛ ይኾናል? በቦታው መገኘት በራሱ፣ በበሬው ለመወጋት አንዱ መዋጮ መኾን አይችልም? ሳላይሽ ኢብሳን ትወደዋለች። ልጅ ተወዶ - ወላጆቹን አለያይቶ - ወንድ ወደሽ ጢሙን ጠልተሽ እንደ ማለትም አይደል? በኢብሳ ወላጆች መሀል የሰደደችው መቀስ ግን የምትወደውን ኢብሳን ቆረጠው። ለሳላይሽ መቀስ ዮሴፍና ኀብስት መዋጮ አላደረጉም ማለት ይቻለናል?

ስንዝሮ እና አኪሊዮስ ለኢ-ሟችነት የቀረቡ ናቸው። ቦታን እንጂ ጊዜን መሰናበት የማይቻላቸው ይመስላሉ። ግን አኪሊዮስም ኾነ ስንዝሮ ይሞታሉ። በግሪክ ሚቶሎጂ እንደ ምናውቀው አኪሊዮስ ኃያል ጦረኛ ነበር። ማንም የማይረታው። ይህ የኾነው ግን አኪሊዮስ ገና እምቦቀቅላ እያለ በጦርነት እንደ ሚሞት ትንቢት በሰማችው እናቱ በኩል ነው። እናቱ በልጇ ላይ የመጣውን ደንቃራ ለማስወገድ ስታስስ አንድ መላ ሰማች። ከስቴክ ወንዝ የተነከረ ከአደጋ ሁሉ ይድናል" ተባለች። የአኪሊዮስን ተረከዝ ይዛ ነከረችው። እንደ ተባለውም ካደገ በኋላ በአንድም ጦርነት ቆዳው ሳይፋቅ ድል በድል ኾነ። ገነነ። አንድ ጦርነት ላይ ግን አኪሊዮስ ተረታ። ይኸውም አንድ ወታደር መርዛማ ቀስቱን በአኪሊዮስ ተረከዝ ውስጥ አሰረገ። አኪሊዮስም በፍጥነት ሞተ። ለካስ እናቱ ስቴክ በተሰኘ ወንዝ ውስጥ ስትነክረው ተረከዙን ይዛው ኖሮ፥ ተረከዙን ውኃ አላገኘውም ነበር። የትኛውም ኃያል ድክመት መኖሩ የሚዘየበው በአኪሊዮስ ተረከዝም አይደል? የስንዝሮ ተረከዝ ራሱን በራሱ ማየቱ ነው። ኢል የተሰኘው የእባብ ዝርያ ዘሩን ካፈሰሰ በኋላ እንደሚሞት እያወቀ አርፎ እንደማይቀመጠው ሁሉ፥ ስንዝሮም ዓይኑን በዓይኑ አየ። ተሰናበተ፤ ራሱን ተከቶ።

ዮሐንስ ወላይሶ በመኪና አደጋ በሞት ሲሰናበት ረቂቅ በኤችአይቪ ኤድስ ታሸልባለች። ነጪት ደግሞ ግብሯን ጨርሳ በሰላም የንጋት እጅ ላይ ታርፋለች። የኀያሲዎቻችን ውክል የሚመስለው ዮሐንስ ወላይሶ "… ግባችን በመንፈስም በሥጋም መሰናበት … ነው። … በናኖ ሰከንዶች የምናደርገው ሁሉ የመሰናበት ነው ድርጊት ነው። ሞትን ነው የምንኖረው …" ብሎ የለ?
ስንብቱ ልዩ ልዩ ነው። ጊዜን ብቻ አይደለም። ቦታንም ይሰናበታሉ።

ንጋት በምኒልክ ገመድ ተጎትታ፣ ፍቼን ተሰናብታ፣ አዲስ አበባ ስትከትም፤ - ሳምራዊው ደግሞ ገጤ ከመኾን ብሎ አዲስ አበባን ተሰናብቶ አራስ ተከትሎ ፍቼ ይገባል። ለይኩን ወንድነቱን በገበረላቸው ሰዎች አፍ ሲብጠለጠል የሚወዳትን ሀገር ተሰናብቶ ከአድማስ ማዶ ይነጉዳል። ጂግሳ ለማ ስንቱን ካየበት፣ ስንቱን ካሳየበት ንፋስ ስልክ ይሰናበታል። ደበሌ የመማጸኛ ከተማ ከኾነለት ሻገር ሆቴል በታጣቂዎች አማካኝነት

ተሰናብቶ ወደ ዝዋይ ግድም ካለ ወኅኒ ቤት ይወርዳል። እትዬ እልልታ ጥርሳቸውን ከሚያስጡበት፣ ላስታ በአርምሞ ከምትዋጥበት፣ ምትክ የደግነት ዘንግ ከምትዘረጋበት ጉልት ይሰናበታሉ። ፍኖት አባዲ ሰዓሊውን ወርቁ ዕንቁባሕሪይን እና ሀገሯን ተሰናብታ ሲኞር ሪካርዶን አግብታ ወደ ባሕር ማዶ ትሻገራለች። ቲጊ ከደጃዝማ ጆቴ በቸሮታ ያገኘችውን ሆቴሏን ተሰናብታ ወደ አማኑኤል የአእምሮ ሕሙማን ሕክምና ተቋም ትገባለች። ስንብቱ ይቀጥላል።

የጋሽ አዳም የስንብት ቀለማት ሥነልቦናዊ ንባብንም ይሻል። የቤላ የእንጀራ አባቷ የኾነው አቶ ተስፋዬ በተደጋጋሚ ይደፍራት ነበር። በውጥንቅጥ ለተሞላው ለቤላ ሕይወት የእንጀራ አባቷ ተጠያቂ አይደለምን? በማኅበረሰባችን ውስጥ በቅርብ ዘመድ የሚደፈሩ እህቶቻችን ውክል ናት ማለት እንችል ይኾን? ቹቹ ሴተኛ አዳሪ የኾነችው እናቷ ሶረንን እያየች ስላደገች ነው? ደጃዝማች ጆቴ የተከበሩና ሀብታም ኾነው ሳለ ሴተኛ አዳሪ ጋር መሄዳቸው ለተኮላ ማንነት ያዋጡት መዋጮ ይኖር ይኾን? የደም ተወራራሽነት ስለሌላቸው ከፍተኛ ፍትወታዊ ፍላጎት ከየት መጣ? ከጂግሳ አባት ከአቶ ለማ ወይስ ከአስተዳደጉ (ከደጃዝማች ጆቴ)? ትጊ በልጅነቷ ዳማ የሚባል ወጠምሻ "ከኔ ጋር ተኝታለች" ብሎ ስላስወራባት እና ለትዳር እንደ ማትኾን ሲሰማት (The feeling of low self-esteem) ወደ አዲስ አበባ ተሰድዳ ሴተኛ አዳሪ መኾኗ ውስጥ ሥነ-ልቦናዊ አስተንትኖት አያሻም? የስንቱን የሕይወት ጦር ወሬ እንደ ፈታው ቆጥሮ መጨረስ ይቻላል? የምትክስ የልጅነት ቀንበር የዋዛ ነው? ተስፋዬን ለመተካት አይደል እንዲህ የምትለን? "የማውቃቸው ሴቶች ወይም ልጃገረዶች ዕድሌ ኾኖ ነው መሰለኝ ጨዋታቸው መሀል ወንድማቸውን በስም ያነሳሉ - ፣ ወይ ከመሀል ወንድሜ ይላሉ። ያወንድማቸውና። ወንድሜ ተስፋዬ የሌለበትን ይሄን ባዶ ቦታ ለመሙላት ወይም ለመሻማት … ብዙ ጊዜ የምጫወተው ከወንዶች ጋር ነበር።" የተስፋዬ ምትክ ለመኾን የጣረችው ጥረት ከሴትነት ቅንብብ አውጥቷት የለምን? እንደዚህ ያሉ አጓጉል ቀንበሮች ማኅበረሰባችን ላይ ከፍተኛ የሥነልቦና ጫና አላሳደረምን? ምትክ ያለአባት ማደጓስ ፍካሬ ይፈልግም የለ?

ጋሽ አዳም ደንበኛ ንቡር ጠቃሽ ነው። በእነ ስንዝሮ በኩል ሚቶሎጂያዊ ንቡር ጠቃሽ (Mythological Allusion) ፣ በዮሐንስ ወላይሶ ገጸባሕርይ አማካኝነት ኀዳግ ላይ የሚያነብራቸው አንዳንድ ሐሳቦች ሥነጽሑፋዊ ንቡር ጠቃሽ (Literary Allusion) እና ታሪካዊ ንቡር ጠቃሽ (Historical Allusion) ፣ በምትክ እና በስንዝሮ ልጅ በኩል ያሉ አንዳንድ ትዕምርታዊ ኩነቶች ቅይጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንቡር ጠቃሽ (Mixed Biblical Allusion) ሊባል የሚያስችል በመኾኑ በተቋማት ለሚደረጉ ጥናታዊ ጽሑፍ ኹነኛ ግብዓት መኾን የሚችል ሥራ ነው፡፡ በውሻ፣ ቢራቢሮ እና መሰል እንስሳት ያስቀመጣቸው ፋንታሲ መሰል የብዕር ውጤት በአሊጎሪካዊ (Allegorical) ወይም ጋሽ ዓለማየሁ ሞገስ እንደ ሚሉት ጽላሎታዊ በኾነ መንገድ ለመመርመር ምቹ መኾናቸውን ጥቁምታ መስጠቱ መልካም ነው።

የስንብት ቀለማት እንጀራ ነው ብንል፣ እርሾው የመጀመሪያዎቹ ገጾች ናቸው። እርሾ ይጎመዝዛል። ሽታውም አይስብም። እንጀራው እንጀራው የሚኾነው ግን በእርሾው ነው። የመጽሐፉ ሁለንተና እነዚህ የመጀመሪያ ገጾች ናቸው። ሁሉም ሰው አንብቦ ከጨረሰ በኋላ ወደ እነዚህ ገጾች ተመልሶ መጥቶ ማንበብ አለበት ባይ ነኝ። የጋሽ አዳም የመጀመሪያዎቹ ገጾች ወንፊትም ናቸው። ትክክለኛ አንባቢውን ከመንገደኛው ማጥለያ ገጾች ናቸው። ዝግ በር ነው። የቻለ የሚከፍተው። ያልቻለው "ውስጡ ያለውን ወርቅ ማግኘት ስለሚቸግረው በከንቱ እንዳይለፋ በጊዜ የሚመልሰው ነው።